ምስክር፡ እግዚአብሔር በእናንተ ይናገራል

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ማቴዎስ 10:16-20

አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ፥ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ፤ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፥ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።—ማቴዎስ 10:19-20

ከበርካታ ዓመታት በፊት በስብከት ሰዓት የተጠቀምኩትን አንድ ምሳሌ በቅርቡ አንድ ሰው አስታወሰኝ። ከዚያን በሓላ ለረጅም ግዜ ለልጆቻቸው ብዙ ጊዜ የነገሯቸው ጠቃሚ ምክር እንደሆነ ነገሩኝ። ምሳሌው ከድርጊታችን ውጤት ጋር የተያያዘ ነበር- የእንጨትን አንዱን ጫፍ ካነሳህ ሌላውንም ማንሳትህ አይቀርም። ነጥቡን ለማስረዳት ትክክለኛ ዱላ እንደተጠቀምኩ ነገሩኝ።

ግን ያንን ምሳሌ ሆነ ዱላውንም መጠቀሜን እንኳ አላስታውስም። ባላስታውስም፤ ነገር ግን ስዕሉ ጠቃሚ ስለነበር ምስጋናዬን ገለጽኩለት።

የዛሬ የቃል ምንባባችን መንፈስ ቅዱስ በጣም በሚያስፈልገን ጊዜ የምንናገረውን ቃል እንደሚሰጠን ጌታ ስለገባው ቃል ይናገራል። ስደት በሌለበት ሁኔታም ቢሆን ይህ እውነት ነው ብዬ አምናለሁ። በመንፈስ ቅዱስ ከተደገፍን እግዚአብሔር በሌሎች ልብ ውስጥ ህይወትን፣ ማበረታታን እና እምነትን ለመፍጠርና ለማንቀሳቀስ ቃላችንን ሊጠቀም ይችላል። እግዚአብሔር ምንም እንኳ የተናገርነውን ሁሉ ባናስታውስም ሰው እየፈለገ ያለውን የልብ መሻት እና ፍላጎት ለመመለስ ቃላችንን ሊጠቀም ይችላል።

በስደት ውስጥ እያለፍን ከሆነ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲሰጠን እንጸልይ። በዕለት ተዕለት ንግግራችንም ዝግጁ እንድንሆን ስለ ቸርነቱ መመስከርን እንለማመድ።

*አባት ሆይ፣ ባንተ ስላላቸው እምነት እየተሰደዱ ላሉ አማኞች እንጸልያለን። የሚናገሩትን እና የመንፈስክን ጥንካሬን ስጣቸው. ስለ መልካምነትህ ስንመሰክር ሁላችንንም ምራን። ኣሜን!*

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድህረገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ምስክር፡ ሁሉም ሰው እንዲቀበል ሞግቱ!

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ሉቃስ 14:15-24

ጌታውም ባሪያውን። ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጣና ይገቡ ዘንድ ግድ በላቸው፤ —ሉቃስ 14:23

ባለፈው ሳምንት ባስተላለፍነው የማለዳ የጥሞና መልእክት ምሳሌ እንመለስ፤ ይህንን ታሪክ በምስክርነት ጥሪያችን መነጽር ማሰላሰል እንችላለን። በኢየሱስ ምሳሌ ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ሥዕሎች አንዱ የታላቅ በዓል እንደሆነ እናስታውሳለን።

እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በሰርግ ድግስ ሥዕል ይዘጋል። ኢየሱስ አንድ ቀን ተመልሶ ይመጣል፣ እናም የተበላሸው ነገር ሁሉ ይስተካከላል። በራዕይ 19፡9 ላይ "መልአኩም ይህን ጻፍ አለኝ፦ ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው!" በጉ ኢየሱስ ነው። እና እንግዶቹ ለእርሱ ግብዣ አዎን ያሉት ሁሉም ናቸው።

በዚህ የሉቃስ መልእክት ውስጥ፣ ኢየሱስ ያንን ታላቅ በዓል ስንጠብቅ ጥሪያችን የሚመጣውን ሁሉ እንድንጋብዝ እንደሆነ ነግሮናል። ይህ የኢየሱስ ምሳሌዎች ማእከል ነው። እያንዳንዱ ወንበር እንዲሞላ በጥልቅ ይናፍቃል። አገልጋዮቹን "ሂዱና ያገኛችሁትን ሁሉ አምጡ" ብሏቸው ነበር። አገልጋዮቹም ያን ባደረጉ ጊዜና ቦታ ሲቀር እንደ ገና ላካቸው።

እግዚአብሔር በድግሱ ጠረጴዛ ዙሪያ ቦታ እንደሰጣቸው የሚገልጸውን አስደሳች ዜና ለመስማት ማበረታታት የሚያስፈልጋቸውን የምታውቋቸውን ሰዎች ሁሉ አስቡ። ጌታ ሁሉንም ሰው ጋብዟል - ቃሉን አታስተላልፉም? እና እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ቸርነት ሁሉ የሚፈልቀውን ልግስና እንዴት ማካፈል ትችላላችሁ?

ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ወደ ግብዣህ ስለተጠራሁኝ በብዙ ምስጋና እና ደስታ እሞላለሁ፣ ሌሎችም እንዲመጡ መጋበዝ እንድችል ጸጋህ በድፍረት እንዲሞላኝ እለምንካለው። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድህረገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ምስክር፡ ብርሃኑን አንጸባርቁ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ዮሐንስ 1: 1-8

ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ፥ እርሱ ብርሃን አልነበረም። —ዮሐንስ 1:8

እምነታችንን ስለማካፈል ስናስብ፣ የምንናገረውን ትክክለኛ ቃል ለማግኘት ብዙ ጊዜ እንጨነቃለን። የተሳሳተ ነገር ብናገርስ? አንድ ሰው እንዴት እንደምመልስ የማላውቀውን ጥያቄ ቢጠይቀኝስ? ምስክርነቴ ምን አይነት ይሆን?

የዮሐንስ ወንጌል የመጥምቁ ዮሐንስን ሥራ እንዴት እንደሚገልጽ እወደዋለሁ። ለኢየሱስ ወንጌላዊ (መልእክተኛ) መሆን ምን ማለት እንደሆነ የሚያረጋግጥ መግለጫ ነው። ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ ብርሃንነት ሊመሰክር እንደ መጣ ተነግሮናል። "እርሱ ብርሃን አልነበረም፣ ለብርሃንም ምስክር ሊሆን መጣ እንጂ" የሚለውን ጠቃሚ ማብራሪያ ነው።

አሁን የትም ቦታ ብትሆኑ በአቅራቢያዎ ያለውን ቅርብ የሆነውን ብርሃን ተመልከቱ። ይህን ማድረግ ለዓይንዎ በጣም ምቹ ላይሆን ይችላል። በአጠቃላይ መብራቶች የተሰሩት እንድናያቸው አይደሉም፤ የብርሃን አላማ በዙሪያው ያሉትን ነገሮች መግለጥና ማሳየት ነው። ለምሳሌ አንድ ዓይነት ብርሃን እነዚህን ነገሮች እንድታይ እየረዳህ ስለሆነ መጽሐፍ ማንበብ እና በዙሪያህ ያሉትን ነገሮች ማየት ትችላለህ።

ስለ ኢየሱስ ሊመሰክር የመጣው የመጥምቁ ዮሐንስ ሚና ሰዎች ስለ ብርሃን እንዲረዱ መርዳት ነው። ዮሐንስ ብርሃኑ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ ብርሃን የሆነው አምላክ ሕይወት ምን እንደሆነ ለማወቅ የሚያስችል መሆኑን እንዲገነዘቡ ረድቷቸዋል። በተመሳሳይም ስለ ኢየሱስ የምንመሰክረው ስለ ራሳችን ሳይሆን ሰዎችን የዓለም ብርሃን ወደሆነው አምላክ ለመጠቆም ነው።

የዓለም ብርሃን የሆነው ኢየሱስ ዛሬ በልባችን ያበራል። አምላካችን ሆይ የፍቅር እና የተስፋ ብርሃንህን በሚናፍቅ አለም ውስጥ ስለ አንተ በታማኝነት እንድንመሰክር እርዳን። አሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድህረገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ምስክር፡ እኔ? ወንጌላዊ?

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ዮሐንስ 4: 1-26

ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች። ኢየሱስም፤ ውኃ አጠጪኝ አላት፤— ዮሐንስ 4: 7

ብዙ ክርስቲያኖች የወንጌልን መልእክት ለማካፈል ይቸገራሉ፤ የተሳሳተ ነገር መናገር ወይም ሰዎችን ማስከፋት ወይም መገፋፋት አንፈልግም። በአንድ ወቅት ቤት ለቤት የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ስሰራ ምን ያህል እንደፈራሁ አስታውሳለሁ። በአሥራዎቼ ዕድሜ ውስጥ ሳለሁ በአንድ ሰፈር ቤት ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ወጣቶች ጋር በበጎ በፈቃደኝነት አብሬ አገለገልኩ። በአቅራቢያችን ለሚኖሩ ልጆች የዕረፍት ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንመራ ነበር፣ እና ከልጆች ቤተሰቦች ጋር ለመጠየቅ ስንከታተል በጣም ከመጨነቅ የተነሳ አንዳንድ ጊዜ የምናገለግለውን የቤተ ክርስቲያንን ስም ይቅርና እምነታችንን እንዴት እንደምንካፍል! እንረሳው ነበር፤

ያ የስብከተ ወንጌል መንገድ ዛሬ ውጤታማ ያለመሆን አዝማሚያ ሊኖረው ይችል ይሆናል። ብዙ ሰዎች ከሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር እና እንደ ጓደኛ መመስከር የበለጠ ፍሬያማ እንደሆነ ተገንዝበዋል።

ዮሐንስ 4 ኢየሱስ በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ከአንዲት ሴት ጋር እንዴት ንግግር እንዳደረ ይነግረናል። ከማያውቃት ሴት ጋር መነጋገሩ በባህሉ ያልተለመደ ነበር፣ ነገር ግን ለእሷ እና ለህይወቷ ያለውን ልዩ ሐሳብ ተረድታ ነበር። ኢየሱስ ደፋር እና ግንኙነቱ መልካም እና ደግ ነበር። ከእሱ ጋር ስታወራ፣ አሳቢ ነገር ግን የቆሰለችና ግንኙነቷ የተቋረጠ ሰው መሆኗን አሳየች።

ምሥራቹን የምንሰብክባቸው አብዛኞቹ ሁኔታዎች እንዲህ ዓይነት ፈጣን ለውጥ አያመጡም። ነገር ግን የኢየሱስን የርኅራኄ አቀራረብ መከተል፣ የሰዎችን ታሪክ በማዳመጥ፣ ወደ ሕመማቸው መግባት፣ እና ስለሚወዳቸው አምላክ በየዋህነት እና በአክብሮት መናገር እንችላለን።

አባት ሆይ፣ ከሌሎች ጋር ያለኝን ግንኙነት የበለጠ በትኩረት እንድከታተል በቅዱስ መንፈስህ አስታጥቀኝ። በርህራኄህ እንድመሰክር እና ለምጠየቀው ጥያቄ እንድመልስ እርዳኝ። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድህረገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ምስክር: ልረዳው አልችልም!

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — የሐዋርያት ሥራ 4:8-20

እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው። — የሐዋርያት ሥራ 4:20

አንድ ያልተለመደ ነገር ስናይ ወይም ሲያጋጥመን አብዛኛው ጊዜ ስለ ጉዳዩ ለሰዎች አለመናገር አንችልም። ከታዋቂ ሰው ጋር መገናኘትም ሆነ አስደናቂ የእረፍት ጊዜ ወይም ህይወትን የሚለውጠውን ክስተት ልናካፍለው እንፈልጋለን። በወጣትነቴ፣ ከመጀመሪያዎቹ የጠፈር መንኮራኩሮች መካከል አንዱን ለመብረር ሲነሳር አይቻለሁ። ወደ ቤት ስመለስ ሁሉንም ጓደኞቼን እንደነገርኳቸው እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ!

በዚህ ሳምንት፣ ስለ እግዚአብሔር ትልቅ ተልዕኮ ስናስብ፣ በሁለተኛው ቃል ላይ እናተኩር፣ ምስክር። ስለ እግዚአብሔር የማዳን ሥራ እንመሰክራለን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ይህን እንድናደርግ ስለጠራን እና መንፈስ ቅዱስ ሊረዳን ስለመጣ (የሐዋርያት ሥራ 1፡8) ።

ውስጣችንም ደግሞ ይነሳሳል። የእግዚአብሔርን የማዳን ፍቅር እና ሃይል ከተለማመድን እና ማንነታችንንና አኗኗራችንን ሙሉ በሙሉ ከለወጠው እንዴት ስለሱ አንናገርም?

በዛሬው ምንባብ ሐዋርያቱ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሽባ የነበረውን ሰው በመፈወሳቸው የተነሳ በኢየሩሳሌም ባሉ የሃይማኖት መሪዎች መካከል ሁከት እንደፈጠሩ እናነባለን። እነዚያ መሪዎች ይህን ፈውስ በየትኛው ኃይል ወይም ሥልጣን እንደፈወሱ ማወቅ ፈልገው ነበር። ጴጥሮስ፣ እንደቀድሞው በድፍረት፣ ኢየሱስን እና ኢየሱስን ብቻ እንደሚያገለግሉ ተናግሯል። ስለ ኢየሱስ የመናገር እና በስሙ የማገልገል ስራቸውን በተመለከተ፣ ከአዳኙ የተማሩትን ሁሉ ከማካፈል እንዴት ይቆጠባሉ? እንደዚሁም ህይወታችን በመዳናችን ደስታ ይፍሰስ!

አባት ሆይ፣ ይህ ክፍል እንደሚያስታውሰን፣ ከአንተ በቀር "መዳን በሌላ በማንም የለም"። በታላቅ ፍቅርህ የተነሳ የአንተ በመሆኔ ሕይወቴ በደስታ ይፍሰስ። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድህረገጽ ተወስዶ የተተረጎመ